በጀርመን የኢትዮጵያዊያን የዉይይትና ትብብር መድረክ
Ethiopian Forum for Dialogue and Cooperation in Germany
Äthiopisches Forum für Dialog und Zusammenarbeit in Deutschland

---

# ድጋፋችን ከማረጋጊያ ንግግሮች ባሻገር እስከ መሰረታዊ ለውጥ ነው!

በውድ እናት አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ሰፍኖ የሕግ ልእልና ተረጋግጦና የዜጎች እኩልነት አብቦ ለማየት ለበርካታ አስርተ ዓመታት ሕዝባችን በአገራችን ከተሞችና ሽንተረሮች፣ በውጪ የሚኖረውም ወገናችን በዓለም አደባባዮች በአገራችን ሰፍኖ ከነበረው ጸረ ዴሞክራሲ አምባገነናዊ ዘረኛ አገዛዝን ጋር ታግለዋል፣ አያሌ ወገኖች ደማቸውን አፍስዋል፣ አካላቸውን አጉድለዋል፣ ታሪክ የማይረሳውንም መስዋእትነት ከፍለዋል። በነዚህ በወደቁ የኢትዮጵያ ውድ ልጆች ሰማእትነት በተፈጠረ አገራዊ ግፊት በአገራችን አንዣቦ የነበረውን አገር አቀፍ ጎሳ ተኮር እልቂትና መጠፋፋት ጨለማን ገፎ በገዥው ፓርቲ ውስጥ በተገኙ አገር ወዳድ የለውጥ ሐዋርያት ብርቱ ጥረት የኢህአዴግ አገዛዝ ስርዓት አባላት የህዝብን የልብ ትርታ በማዳመጥ ጥያቄውን ለመቀበል ተገደዋል።

በዚህ ታሪካዊ ወቅት ነበር ከገዥው ፓርቲ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድ አዲስ የለውጥ ተስፋን ሰንቀው አገራዊ ማረጋጋትን በመፍጠር ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገር ያለመ ተልኮን ይዘው ብቅ ያሉት:: ይህ በአገራችን የተጀመረው የአዲስ ስርዓት የማዋለጃ ብስራት ተጠናክሮ አገርዊ ፍሬ ያፈራ ዘንድ ትናንት የተጀመረው ትግል በአዲስ አገራዊ ወኔ መትጋትንና መደመርን አንገብጋቢ አድርጎታል:: የአዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ሕልምና ራእይ የመቶ ሚሊዮን ሕዝብ ራዕይ ነው:: የውድ ኢትዮጵያ ልጆች አኩሪ ገድል ውጤት ነው:: የእስካሁኑ ድል በዜጎች ሁለንተናዊ ድጋፍና ትግል ካልታገዘ የምንፈልገውን አገራዊ ለውጥ ሊያመጣ አይቻለውም:: ስለዚህም በገዥው ፓርቲ ውስጥ ያሉ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች የጀመሩትን የለውጥ ሂደት ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድ ጋር እጅና ጓንት በመሆን ጠንከር ያለ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ ከሕዝባቸው በሚሰጣቸው ሁለንተናዊ ድጋፍ እየታገዙ የለውጥ እርምጃውን መግፋቱ ብቸኛውና አማራጭ የሌለው መንገድ መሆኑን በጀርመን የኢትዮጵያውያን የውይይትና ትብብር መድረክ አባላት እናምናለን።

መሰረታዊ ለውጥ አብሮ መቆምና መቻቻልን ይጠይቃል፣ የሽግግር ወቅትም ጤናማ ማድረግ የሚቻለው ብሄራዊ መግባባትና መቻቻልን የፈጠርን እንደሆነ ብቻ ነው:: ይሄን ከልብ እውን ለማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ እስካሁን ያሳዩት የመሪነት ብቃት የበለጠ አገራዊ ተስፋችንን አጠናክሮታል:: ይሄንን በአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር የተጀመረውን ተስፋን የሰነቀ የእርቅና የሰላም ጉዞ ለማደናቀፍ ያለፈው አልበቃ ብሎ፣ ጎሳ ተኮር ግጭቶች እንዲቀጣጠሉ፣ ያንዣበበው የሰላም አየር እንዲደፈርስ፣ ሁከትና አለመረጋጋት እንዲሰፍን የሚታክቱ በማንኛቸውም ጎራ የተሰለፉ የሽብር ጥቃት የሚያራምዱ ፀረ ሰላም ኃይሎች ከድረጊታቸው እንዲቆጠቡ በዚህ አጋጣሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በአገር ጉዳይ አመስጋኝና ተመስጋኝ ባይኖርም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድና በዙሪያቸው ያላችሁ ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ዜጎች ለወሰናችሁት ውሳኔና ለያዛችሁት ትክክለኛ አቅጣጫ በጀርመን የኢትዮጵያውያን የውይይትና ትብብር መድረክ አድናቆቱን እየገለጸ ለሚደረገው አገራዊ መሰረታዊ ለውጥ ምንጊዜም ድጋፋችን አይለያችሁም::

**Email:** ethiopianforumfordialogue@gmail.com **Tel. Nr.:** +4915773912794 or +491782844931
**Adresse:** Mainzer Landstraße 504, 65933 Frankfurt am Main

*በዚህ አጋጣሚ በውጭ አገር በአንጻራዊ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የምንገኝ ዜጎች በአገር ውስጥ እየተካሄደ ላለው ለውጥ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንድናደርግ እያሳሰብን በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድ የሚመራውን የለውጥ ሃይል ለማጠናከር እንድንሰራ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።*

*የኢትዮጵያ ሕዝብም ከምንጊዜውም በላይ እጅ ለእጅ በመያያዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ  የጀመሩትን የመሰረታዊ ለውጥ ትግል እንድታግዙ ስንጠይቅ ትናንት እንዳደረግነው ሁሉ በጀርመን አገር የምንገኝ ውድ ልጆችህ የስልጣን ምንጭነትህና ባለቤትነትህ እስከሚረጋጥ ትግላችን ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ልናረጋግጥልህ እንወዳለን::*

*ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ብሄራዊ እርቅና ብሄራዊ መግባባት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፣ እውነተኛ የብዝሃተ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፣ በውጪ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊነትን ማዕከል ባደረገ ብሄራዊ አጀንዳ ዙሪያ መሰባሰብ  አለባቸው፣ ይሄም የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። አገራዊ ለውጥ እንዲመጣ መቃወም ብቻ ባህላችን ባለመሆኑ በመንግስት በኩል በጎ ተግባራት ሲፈጸሙ ድጋፍ ማድረግም ከእኛ ስለሚጠበቅ በጀርመን የኢትዮጵያውያን የውይይትና ትብብር መድረክና የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራትና አገር ወዳድ ዜጎች በጋራ የሚያዘጋጁት ቅዳሜ ጁላይ* 21 *ቀን* 2018 *በፍራንክፈርት ከተማ የድጋፍ ሰልፍ ለማካሄድ ታስቧል። በቅርቡም ይህንኑ አስመልክቶ የተዘጋጀ ፖስተር ይሰራጫል።*

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!*

*በጀርመን የኢትዮጵያውያን የውይይትና የትብብር መድረክ*